በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት

L011.3/672/2-1

03 መጋቢ 2000

ለኢዴአፓ- መድህን

አዲስ አበባ፣

በመጪው ሚያዚያ ወር ለሚካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሚያካሂዱት የምርጫ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ነፃ የአየር ሰዓት መደልደሉ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረትም ኢዴአፓ-መድህን በመጋቢት 3 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲተላለፍ ባመጣው የምርጫ ቅስቀሳ ፅሁፍ ላይ "በ1997 ዓ.ም በሀገራችን የተካሄደው ምርጫ ጉድለቶች የታዩበት ከመሆኑም በላይ፣ ዓለም አቀፍ የምርጫ አፈፃፀም መርሆዎችን በጣሰ አሠራር ኮረጆ ተቀዶ የሕዝብ ድምፅ የተሰረቀበት እንደነበር የምርጫ ታዛቢዎች ጭምር ምስክርነት የሰጡበት እንደነበር ይታወሳል።" ይላል።

ይህ አገላለፅ በቀድሞ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀፅ 71 እና 72 በድምፅ አሰጣጥ ወቅት ስለሚነሱ አቤቱታዎች አቀራረብ በግልፅ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ፓርቲ ቅሬታውን በወቅቱ ለሚመለከተው የምርጫ ፅ/ቤት እና ለመደበኛ ፍርድቤቶች በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግገዋል።

ይሁንና ይህንን በሕግ የተሰጠ መብት በወቅቱ በአግባቡ የመጠቀም አሁን አቤቱታውን ያቀረበው የኢዴአፓ-መድህን ፓርቲ መብት ነበር። ይህ ሆኖ እያለ ከሕግ አግባብ ውጪ አሁን ባለንበት ሂደት ላይ ይህን ጉዳይ ማንሳት የምርጫ ቦርዱን ሥም እንደማጥፋት ይቆጠራል። የፖለቲካ ድርጅቶችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 4/2000 ዓ.ም አንቀፅ 14 ተራ ቁጥር 3 "ሐ" ላይ "ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት በሀሰት ሥም ማጥፋትና የውንጀላ ፅሁፍ ማተም ማሠራጨት ወይም ንግግር ማድረግ የለበትም"። ይላል